## ከአፋኝና ፈላጭ ቆራጭ ርእዮተአለም ወጥመድ ወጥተን ወደነፃነትና የፍትህ ስርአት ሽግግር—አማራጭ የሌለው የወቅቱ ጥያቄ

**ከድልበቶ ደጎዬ ዋቆ ፣ 15/01/2011**

በ19ኛውና በ20ኛው መቶ ክፍለዘመን በአለም ከተቀነቀኑት አፋኝና ጠቅላይ አይዲዎሎጂዎች መካከል ኮሙኒዝም፣ ፋሺዝም፣ ሰው—በላ ካፒታሊዝም (predator capitalism) እና አብዮታዊ ዴሞክራሲ ተዛማጅነት ያላቸው ዋናዎቹ ርእዮተአለሞች ናቸው። የሰውን ልጅ ለምድራዊ ገነት እናበቃለን እያሉ የሚያማልሉና ባዶ ተስፋ የሚያደርጉ ሆኖ ሳለ በተቃራኒው ለሰው ልጅ ክቡር ህይወት ደንታ የሌላቸው ጨፍጫፊ ርእዮተአለሞች ናቸው። እነዚህን ርእዮተአለሞች ገቢራዊ ለማድረግ የሞከሩት አገዛዞች ሁሉ በብዙ ሚሊዮን ዜጎች የደም ጎርፍ የታጠቡ ጨካኝ መንግስታት ነበሩ። የነርሱን ጠቅላይነት የሚቃወሙትን አስተሳሰቦች፣ ቡድኖችና ግለሰቦችን በጭፍን ጠላትነት ፈርጀው ከመደምሰስ ያልተቆጠቡ አገዛዞች ነበሩ። ኮሙኒስቱ እስታሊን በሶቪየት ህብረት 30 ሚሊዮን ዜጎችን ልዩ ልዩ ስያሜዎችን እየለጠፈባቸው ፈጅቶአቸዋል፣ ፋሺስቱ ሂትለር ከ6 ሚሊዮን የሚበልጡ አይሁዶችንና ሌሎች ማህበረሰቦችን ጨፍጭፎአቸዋል፣ የኛዎቹ አብዮታዊ ዴሞክራቶች ማለትም ደርግና ኢህአዴግ በዘመነ—አገዛዛቸው በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን እንደፈጁ ለማስተባበል አይቻልም። በዚህ ረገድ፣ የካፒታሊዝም አይዲዎሎጂም የተሻለ ታሪክ የለውም፣ ከብዙ አስከፊ ገፅታዎቹ መካከል ኢምፔሪያሊዝም፣ ግዙፍ የባሪያ ፍንገላና የባሪያ ንግድ፣ የቅኚ አገዛዝ ወረራና የህዝቦች የዘር ፍጅት(Genocide)፣ ወዘተ በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው። ይህ በዚህ እንዳለ ሆኖ፣ ከላይ የተጠቀሱት አፋኝ ርእዮተአለሞች ዛሬ በ21ኛው መቶ ክፍለዘመን ሁሉም በልማትና በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ የዳበሩ አገሮች ለህዝቦቻቸው ያጎናፀፉዋቸውን የንግግርና የማሰብ ነፃነትን፣ የህግ የበላይነትን፣ የሰብአዊ መብቶች መከበርን፣ ነፃ ምርጫዎችን፣ ፍትህን፣ የኢኮኖሚ ነፃነትን፣ የመድበለ—ፓርቲ ስርአትን፣ የግል ንብረት መብትን፣ ወዘተ የማያስተናግዱ ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱትን ታሳቢዎች መነሻ በማድረግ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ የኢትዮጵያን ህዝብ ፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትና ልማት አጎናፅፋለሁ የሚል ተስፋ ሲለፍፍ የሰነበተ ቢሆንም ባለፉት 27 አመታት በግዙፍ የውጭ እርዳታና ብድር ላይ ጥገኛ ያልሆነ ዘላቂ ልማት ሊያስገኝልን ካለመቻሉም በላይ በተጫነብን አፋኝና ጠቅላይ አገዛዝ፣ የስቃይና የመከራ  ሁኔታ አገዛዙ ለምን ተፍረክርኮ ወደመበስበስና ወደውድቀት እንዳመራ እንዲሁም ዛሬ ከፊታችን ፈንጥቀው የወጡትን የለውጥና የነፃነት ተስፋዎችን ፋይዳ ባጭሩ ከዚህ ቀጥሎ ለመዳሰስ እሞክራለሁ። ከሁሉም በላይ ስለማንኛውም ርእዮተአለም የምናካሂደውን የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ከንቱ ክርክር አቁመን ሰብአዊ እሴቶችን ለማስፋፋት ቁርጠኛ አቋም በማድረግ ላለፉት አራት አስርተ አመታት (ከደርግ እስከ ኢህአዴግ) የተጫነብንን የአብዮታዊ ዴሞክራሲን የአፈና ወጥመድ አሽቀንጥረን ጥለን ከላይ እንደተጠቀሰው ለሰው ልጅ ህይወት ክቡርነት (the sanctity of human life) የቆሙትን ሰብአዊና ሞራላዊ እሴቶች በማዳበር ሰላም፣ ደህንነት፣ ፍትህ፣ ነፃነትና ብልፅግና ወደሚያሰፍን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመሸጋገር ያለማሰለስ ብርቱ ተጋድሎ የምናደርግበት የሽግግር ወቅት ላይ እንደምንገኝ ለማስገንዘብ እሻለሁ።

ላለፉት 27 አመታት በመላ አገሪቱ የተዘረጋው የህወሀት—መራሹ የኢህአዴግ አገዛዝ ሲከተለው የነበረው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አይዲዎሎጂ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የጫነበት የአምባገነንነት፣ ከመሬትና ከመኖሪያ ቤት የማፈናቀል ግፍ፣ የነፃነት አፈና፣ የጅምላ ግድያ፣  የከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ፣ የአካል ማጉደል፣ የሰቆቃና የቡድን ዝርፊያ  አገዛዝ ያንገሸገሸው ሰፊው ህዝብ በተለይ ከ2008 አም አንስቶ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣

በደቡብ፣ በአፋር፣ በሱማሌ፣ በቤንሻንጉል፣ በጋምቤላ፣ ወዘተ ክልሎች የተቀጣጠሉትን ሰላማዊ የህዝባዊ እምቢተኝነት እንቅስቃሴዎችና ካለፉት ጥቂት አመታት ወዲህ በተንሰራፋው የባለስልጣኖችና የተባባሪዎቻቸው ገደብየለሽ ሙስናና የኪራይ ሰብሳቢነት የተነሳ ሊያሽቆለቁል የተገደደውን የኢኮኖሚ እድገት ተከትሎ የደረሰበትን ከፍተኛ ጫናና ግፊት ለመቋቋም ባለመቻሉ የኢህአዴግ መራሹ አገዛዝ እየተሸረሸረና እየተዳከመ ሄዶ ወደማይመለስበት መንግስታዊ ውድቀት (state failure) ተቃርቦ እንደነበር ሁላችንም በከባድ ስጋት፣ ሀዘንና ጭንቀት የታዘብነው እውነታ ነበር። ይፍጠንም ይዘግይ፣ መንግስት አልባ ሆነን ወደከፋ ስርአተ—አልበኝነት፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች ውስጥ እንደምንዘፈቅ የሚተነብዩ "ነቢያት" ከሩቅም ከቅርብም በብዛት ነበሩ። ሆኖም፣ ይህንን ከፍተኛ አደጋና የመላውን ህዝብ የማያወላውሉ የነፃነት፣ የፍትህና የእኩል ተጠቃሚነት ጥያቄዎችና ፍላጎቶች በትክክል የተገነዘቡ የኢህአዴግ አመራሮች የተለመደውን "ጥልቅ ተሃድሶ" ባደረጉበት ሂደት እነለማ መገርሳ፣ ዶ/ር አቢይ አህመድ፣ ደመቀ መኮንን፣ ገዱ አንዳርጋቸውና ሌሎችም የለውጥ ደጋፊዎች ከበስተጀርባቸው ከባድ የደም ዋጋ ከፍለው በተሰለፉላቸው የወጣቶች ድጋፍ (በዋነኝነት "ቄሮዎች"፣ "ፋኖዎች" እና "ዘርማዎች") የኢህአዴግን ወሳኝ የአመራር ሚና በመቀዳጀት ድርጅቱንም ሆነ አገሪቱን ለመታደግ የሚያስችሉ የለውጥ እርምጃዎችን በአፋጣኝ ለመውሰድ በቁርጠኝነት ተንቀሳቀሱ፣ ኢህአዴግን እንደተንኮለኛ እባብ በመቁጠር ከድርጅቱ የሚወጡትን በጎ መግለጫዎች ሁሉ ባለማመን "ከእባብ እንቁላል የእርግብ ጫጩት ሊፈለፈል አይቻለውም" ሲሉ ለቆዩት ሃያሲያንና ተቺዎች እነዶ/ር አቢይ አህመድና ለማ መገርሳን የመሳሰሉ መሪዎች ከኢህአዴግ ጉያ ብቅ ብለው ስርነቀል ለውጥ ለማካሄድና ወደነፃነትና ወደፍትሃዊ የመድበለ—ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማሸጋገር በይፋ ሲያውጁ ለብዙዎቻችን ታዛቢዎች በቶሎ ለማመን አዳጋች ሆኖብን እንደነበር ለመገመት አያስቸግርም ነበር ። ነገር ግን ዶ/ር አቢይ አህመድ የኢህአዴግ ሊቀመንበርነትና የጠቅላይ ሚኒስትርነት ስልጣን በቃለመሃላ ከተረከቡ ካለፉት ጥቂት ወራት ወዲህ የተስፋ ቃላቸውን ጠብቀው የማይታመኑ የሚመስሉ ፈጣንና ዘርፈብዙ ተግባሮችና እንቅስቃሴዎችን በመፈጸም ለእኛ ከደርግ ዘመን አንስቶ በአፈና ስርአት ላለፉት 44 አመታት ያሳለፍን ኢትዮጵያውያን ብሩህ የተስፋ ዘመን የሚያጫሩ የተሃድሶ ንቅናቄዎችን አስጀምረዋል።

የአፈና ስርአቱን በመበጣጠስ የነፃነት ጎህ ቀደዱልን፣ ባለፉት 40 ያህል አመታት ለመጀመሪያ ጊዜ የነፃነት አየር ለመተንፈስና እፎይ ለማለት በቃን። ቀጥሎም ዶ/ር አቢይ አህመድና ጓዶቻቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የፖለቲካና የህሊና እስረኞችን ከተለያዩ የማጎሪያ እስር ቤቶች በይቅርታ እንዲወጡ አደረጓቸው (ገራፊ ወንጀለኞችን ለፍርድ የማቅረቡና የማስቀጣቱ ሂደት ገና የቤት ስራ ሆኖ ቢዘገይም)፣ በተከታታይም ወደጅቡቲ፣ ወደኬንያ፣ ወደሱዳን፣ ወደሳኡዲ አረቢያ፣ ወደግብፅና ወደመካከለኛው ምስራቅ በመጓዝ ኢትዮጵያውያን እስረኞችን በሙሉ አስፈቱ። የመከላከያ፣ የፖሊስ፣ የደህንነትና የእስር ቤቶች ተቋማትን ለለውጥ አመቺ በሚሆኑበት አቋም እንደገና እንዲደራጁ አደረጉ፣ ወደጡረታ የሚወጡትን ወታደራዊና የሲቪል ባለስልጣኖችን ወደጡረታ አስወጡ። የምህረት አዋጅ እንዲታወጅ በማድረግ በሽብርተኝነት ተፈርጀው የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች በወንጀል ተከስሰው የተፈረደባቸውን ዜጎች የአዋጁ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አበቋቸው። ቀጥሎም፣ የዳያስፖራ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ተቃዋሚም ሆኑ ደጋፊዎች ወደአገራቸው ገብተው በነፃነት በማንኛውም ዘርፍ ተሳታፊ እንዲሆኑ የዘንባባ ዝንጣፍና የሰላም ጥሪ ከማቅረባቸውም በላይ ወደአሜሪካ በመጓዝ በተለያዩ ከተሞች ያሉትን ኢትዮጵያውያን ከማሳመናቸውም በላይ እርስ በእርስ እንዲታረቁ፣ እንዲደጋገፉና በኢትዮጵያዊነት ዜግነትና ማንነታችን ዙሪያ በአንድነት እንዲቆሙ በአፅንኦት አደራ በማለት ወደአገራቸው ለመመለስ በቅተዋል፣ የአብዛኛዎቹን ዳያስፖራ ኢትዮጵያውያንን ያልተቆጠበ ድጋፍና አድናቆት ተቀዳጅተው ተመልሰዋል፣ ይህ እጅግ ደስ የሚያሰኝ የዶ/ር

አቢይ አህመድ ዲፕሎማሲያዊ ድል ነው ። በዚህም የተነሳ ከመላው ህዝባችን (ከወጣቱም ሆነ ከአረጋውያን፣ ከሴቱም ሆነ ከወንዱ፣ ከክርስቲያኑም ሆነ ከሙስሊሙ፣ ከዳያስፖራውም ሆነ ከአገር ቤቱም፣ ወዘተ) የተሰጣቸው ድጋፍ መሬት አንቀጥቅጥ እንደሆነ ለማረጋገጥ ችለናል፣ ነገር ግን አሁንም አንዳንድ ተቃዋሚዎች በተለያዩ ክልሎች መኖራቸውን ደግሞ ለመካድ አይቻለንም።

ከሁሉም በላይ ደግሞ እጅግ አንገብጋቢ ጉዳዮች እፊታችን ተደቅነዋል። በመጀመሪያ ደረጃ፣ ዛሬ ከ100 ሚሊዮን በላይ የሆነው ህዝባችን በየአመቱ ከ2,6% ገደማ እድገት እያሳየ ባለበት ሁኔታ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወጣቶች በሁሉም ክልሎችና ከተሞች የስራ እድል በማጣት በከንቱ የሚጉላሉበት ሁኔታ በአስቸኳይ መፍትሄ ካላገኘ የለውጡን ሂደትና የኢትዮጵያን ትንሳኤ ለማጨናገፍ ከውስጥም ከውጭም ላሰፈሰፉ እኩይ ጠላቶች በገንዘብ ተገዝተው የነዚህ መሰሪ ተልእኮ መሳሪያና አስፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት እድል ዝግ አለመሆኑን አለማገናዘብና ተገቢ ጥንቃቄዎችን በጊዜ አለማድረግ መሪር ዋጋ ያስከፍለናልና ልብ ያለው መንግስትና ሌላው ወገን ሁሉ ልብ ይል ዘንድ ለማሳሰብ እወዳለሁ። በተጨማሪም የግብርናው ዘርፍ ምርታማነት እጅግ ዝቅተኛ ሆኖ ከማዝገሙም በላይ ገና ስትራክቸራል ትራንስፎርመሽን ለማድረግ ባለመቻሉ የህዝባችንን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልና በምግብ አቅርቦት ረገድ ራሳችንን ለመመገብ አልቻልንም፣ በየአመቱ የምናገኘውን ከፍተኛ የውጭ እርዳታና ብድር ለልማት ብቻ ሳይሆን ለየእለት ፍጆታችን የሚሆኑ ስንዴ፣ ማዳበሪያና ልዩ ልዩ ቆሳቁሶችን ከውጭ አገሮች ለማስገባት ተገድደናል፣ ከ8—10 ሚሊዮን ወገኖቻችን በየአመቱ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ጥገኞች ናቸው፣ ባለፉት ጥቂት አመታት በተለያዩ ክልሎች በተቀሰቀሱት ብሄር—ተኮር ግጭቶች ምክንያት ከ1,4 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ዜጎቻችን ተፈናቅለዋል። በተጨማሪም፣ በሁሉም የአገሪቱ ከተሞች የውሃ፣ የመብራት፣ የመንገድ፣ የሸቀጣ ሸቀጦችና የአገልግሎቶች እጥረትም ሆነ የዋጋ ንረትና የትራንስፖርት ዋጋ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ ይገኛል፣ ለነዚህ ችግሮች አስቸኳይ መፍትሄዎች ካልተበጁላቸው በስተቀር የሚያስከትሉት አደጋዎች እንደዚሁ የከፉ ይሆናሉና ይታሰብበት እላለሁ። በሁለተኛ ደረጃ፣ ባለፉት በርካታ አመታት በተለያዩ እስር ቤቶች ከፍተኛ ግፍ፣ ሰቆቃና መከራ የደረሰባቸው የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ተገቢውን የሞራልና የማቴሪያል ማካካሻ የሚያገኙበት ስልትና ወንጀለኞቹን ለማስቀጣት የሚቻልበት እቅድና ፕሮግራም በአፋጣኝና በግልፅ አለመነደፉ ነው። ይህ አሳሳቢ ፈተና ነው፣ ውሎ አድሮ የሚፈነዳ በምብ መሆኑ አይቀርምና።

የሆነ ሆኖ፣ ባለፉት ጥቂት ወራት ውስጥ ዶ/ር አቢይ አህመድ ያከናወኗቸውን አስደናቂ የሰብአዊ መብቶችን የማስከበር ስራዎችና በዚህም ረገድ ያስመዘገቧቸውን አንፀባራቂ ድሎች (በተለይም ከኤርትራ ጋር ለሀያ አመታት የወገብ ቅማል ሆኖ ሲያሰቃየን ለነበረው የጠላትነት ነቀርሳ አፋጣኝ የሁለትዮሽ ዲፕሎማሲያዊ ድል በማስመዝገብ) የታዘበ ማናቸውም ዜጋ በደስታና በእልልታ የሚያጅባቸው አስደናቂ ክንውኖችና መልካም ጅማሬዎች እንደሚሆኑ ከቶውንም አልጠራጠርም፣ የኔም ስሜት ይሐው ነው። የሆነ ሆኖ፣ ማናቸውም ብሩህ ተስፋ የሚያጎናፅፍ መልካም ጅማሮ ወደመልካም ፍፃሜ ያደርሰን ይሆናል በሚል ተስፋ እንጂ ባሁኑ ወቅት አንዳችም ተቋማዊ ዋስትና ያለው ሁኔታ ገና አልተፈጠረም፣ ገና አልተረጋገጠልንም፣ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት(የፕሬስ ቦርድና የፕሬስ ነፃነት ተቋማት፣ ገለልተኛ የምርጫ ኮሚሽን፣ የሲቪል ሶሳይቲ ማህበራት፣ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ የእንባ ጠባቂ ቢሮ፣ የፈጣን ዳኝነት የፍትህ ተቋማት/ፍርድ ቤቶች፣ ወዘተ) ገና አልተገነቡም፣ ገና ወደዳበረ መድበለ— ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ስርአት አልተሸጋገርንም። የተፍረከረከ ፓርቲም ቢሆን የኢህአዴግ አውራፓርቲ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮተአለም በሚመራ የአምባገነንነት ስርአት ስር አሁንም በሞኖፖል እየገዛን ነው። ይህ በእዚህ እንዳለ ቢሆንም፣ ዛሬ እድሜ ለባለራእዩ መሪያችን አፋጣኝና ተከታታይ በጎ እርምጃዎች የተነሳ የኢህአዴግ የቀድሞ አፋኝና ጨፍጫፊ ተግባሮቹ ቀስ በቀስ እየተወገዱ ናቸው፣ ስያሜው አሁንም ኢህአዴግ

ቢሆንም አረመኔያዊ ተግባሮቹ እየተገረሰሱ ናቸው። ይበል የሚያሰኝ ቆራጥነት ነው፣ ይቀጥል ዘንድም በፅኑ እንሻለን።

ከሁሉም በላይ፣ በመላ አገሪቱ ካለፉት ጥቂት አስርተ አመታት በተለይም ከ2008 አም የግንጪ ወጣቶች አመፅ ወዲህ ባልተቋረጠና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የተቀጣጠሉት የህዝባዊ እምቢተኝነትና የወጣቶች(የቄሮዎች፣ የፋኖዎች፣ የዘርማዎችና ገና ግልፅ ስያሜ ያልወጣላቸው የተለያዩ ክልሎች የዘውግ ወጣቶች) ሰፊ ንቅናቄዎች በአብዛኛው የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶችን የማስከበር፣ የህገመንግስት፣ የህግ የበላይነትና የመንግስት የተጠያቂነት እንዲሁም የመልካም አስተዳደርና የነፃነት ዋስትና የማስከበር ሰላማዊ ትግሎች እንደነበሩ ለመካድ አይቻልም። ለነዚያ ቄሮዎች፣ ፋኖዎችና ዘርማዎች መሪር መስዋእትነት የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ ከበሬታና አድናቆት እንዳለው ከማናችንም የተሰወረ አይደለም። ክርስቲያኑንም ሆነ ሙስሊሙን፣ ወጣቱንም ሆነ ሽማግሌውን ሁሉ ከዳር እስከዳር ያስተባበሯቸው አንገብጋቢ የህልውና ጥያቄዎች የሰብአዊ መብቶች፣ የመሬት ባለቤትነትና የኢኮኖሚ ጥያቄዎች እንደነበሩ መገንዘቡ ለአዲሶቹ መሪዎች የወደፊት የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ፖሊሲ ማሻሻያዎች፣ ቀረፃና የትኩረት አቅጣጫ ያግዛል ብዬ እገምታለሁ።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መለኮታዊ ተሰጥኦ እንዳላቸው ተደርጎ የሚወደሱ መሪዎች (charismatic leaders) ሁሉ ከአማላይ ድስኩሮችና መግለጫዎች ባሻገር ዋስትና ያላቸውን የህግ የበላይነትና የዴሞክራሲ ግንባታ ተቋማዊ መደላድሎችንና ፍኖተ—ካርታ ካልዘረጉ፣ ግልጽ ራእይ ካላመላከቱ፣ እንዲሁም በተለያዩ ክልሎች የተቀጣጠሉትን ብሄረሰብ—ተኮር የእርስ በእርስ ግጭቶችንና መፈናቀሎችን በአስቸኳይ በማስቆም በተረጋጋ ሰላማዊ ሁኔታ ስር ከሁሉም የተፎካካሪ ፓርቲዎችና ማህበራዊ ድርጅቶች መሪዎች ጋር በመወያየትና በመደራደር የወደፊቱን የለውጥ አቅጣጫ የሚያመላክት አስተማማኝ የጋራ ራእይና ፍኖተ—ካርታ (roadmap) በስምምነት ነድፈው የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ በግልፅ ካልተዘረጋ በስተቀር ይዋል ይደር ባልታሰቡ ድንገተኛ ክስተቶች የተነሳ በሚፈነዱ ያልተጠበቁ ደንቃራዎች የተነሳ እነዚህን ለማስወገድ በሚወስዷቸው እርምጃዎች የተነሳ ወደድንም ጠላን ተመልሰው ወደፍፁም አምባገነንነት ሊለወጡ የሚችሉበት አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ እንዲገቡ ሰፊ እድል ስለሚኖራቸው እኛም በዶ/ር አቢይ አህመድ "የመለኮታዊ ስጦታነት አመራር" እና የመልካም ራእይ መግለጫዎች ላይ ብቻ በመተማመን ልንዝናና እና ልንዘናጋ የምንችልበት ሁኔታ አይታሰብም፣ የዶ/ር አቢይ አህመድ መንግስት የመልአክት ሳይሆን የሰዎች አገዛዝ ስለሆነ ፍፁም የሚያስተማምን ሁኔታ ሊያረጋግጥልን አይችልም፣ በየክልሎቹ "በቄሮዎች"፣ "በፋኖዎች"፣ "በዘርማዎችና" በሌሎች የወጣት ቡድኖች ሽፋን በወሮበላዎች የሚፈፀሙትን ህገወጥ ድርጊቶችን በጥሞና የሚታዘብ ዜጋ ለማረጋገጥ እንደሚችለው እነዚህ ግብታዊ የስርአተ—አልበኝነት እንቅስቃሴዎችና ህገወጥ ድርጊቶች በአስቸኳይ ካልተገቱ የምንመኘው የዴሞክራሲና የነፃነት የለውጥ ጉዞ ሊደናቀፍ እንደማይችል አንዳችም ዋስትና አይኖረንም። የእነለማ መገርሳ ቡድን እየተባሉ የሚጠሩትን የለውጥ አራማጆች መሪዎቻችን እነርሱ መሆናቸውን ተቀብለን "ከናንተ አመራር ጋር ወደፊት" ብለን ቃልኪዳን የገባን ዜጎች የተጠቀሱት ቀልባሽና ከላሽ፣ ህገወጥና ጋጠወጥ እርምጃዎች ከመሪዎቻችን በስተጀርባ ሲወሰዱ እየተመለከትን በዝምታ ካሳለፍን ምን ይሆን አላማችንና ግባችን? የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርምና ጠንቀቅ ማለቱ ይበጃል። ጥቂት ምሳሌዎችን ለመጥቀስ፣ ካለፉት ሳምንታት ጀምሮ ከኢሳት የቲቪ ዜና እንደምንሰማው፣ 1/ ከሀረር ከተማ የሚወገደው ቆሻሻ ወደሚወሰድበት የቆሻሻ መቅበሪያ ስፍራ እንዳይጫን በክልሉ መስተዳድር ሳይሆን በ"ቄሮዎች" ውሳኔ ተከልክሏል ተብሏል፣ 2/ አሁንም "በቄሮዎች" ጣልቃገብነት የተነሳ የደርቢ ሲሚንቶ ፋብሪካ ስራውን አቁሟል ተብሏል፣ 3/ የባህርዳር "ፋኖዎች" ከአማራ ክልል ወደትግራይ ሊጓጓዝ የነበረውን እህል የጫነ ተሽከርካሪ በባህርዳር ከተማ ውስጥ

አስቁመው እህሉን ዘርፈዋል ተብሏል፣ 4/የተርጫ—ዳውሮ "ወጣቶች" በፈቃደኝነት ከዳውሮ ወደዱርጊና ዱራሜ የሚወስደውን የገጠር መንገድ በጉልበታቸው ለመስራት የተነሳሱበት እንቅስቃሴ በዞኑ የመገናኛ ብዙሃን አሉታዊ ሽፋን ተሰጥቶታል በሚል ቅሬታ ተነሳስተው በርካታ የዞኑን መንግስታዊ ተቋማትን አውድመዋል ተብሏል፣ 5/ በከፋ ዞን በጨና ወረዳ ማዶ ለማዶ በሚኖሩ አጎራባች መንደሮች ባልታወቀ ምክንያት ያንደኛው መንደር "ወጣቶች" በቁጣ ተነሳስተው የሌላኛውን መንደር በርካታ ቤቶች በአንድ ጀንበር አውድመዋል፣ ንብረቶችን አቃጥለዋል ተብሏል፣ 6/በሸካ ዞንም በቴፒ ከተማ ብሄርን ያነጣጠሩ ከባድ ጥቃቶች ተፈፅመው በርካታ ወገኖች ለከፍተኛ ጉዳቶች እንደተዳረጉ፣ በርካታ ንብረቶች እንደወደሙና እንደተዘረፉ እንዲሁም እስካሁን 2 ሰዎች ስለመገደላቸው ነሃሴ 07/2010 በተላለፈው የኢቲቪ ዜና ተገልፆአል፣ 7/ነሃሴ 06/2010 የኦኤም ቡድን በኦቦ ጃዋር መሀመድ መሪነት ወደሻሸመኔ ከተማ ከደረሰ በሁዋላ እኚህን ታዋቂ አክቲቪስት ለመቀበል በርካታ ሺህ የሚቆጠር ህዝብ በወጣበት ስነስርአት ላይ ማንነቱ ያልታወቀ ግለሰብ "ቦምብ!ቦምብ!" ብሎ በመጮሁ የተደናበረው ህዝብ ወደአመቻው አቅጣጫ በሚሯሯጥበት ወቅት በመረጋገጥ ብቻ አራት ሰዎች እንደሞቱና 8 ሰዎች ደግሞ መቁሰላቸው አልበቃ ያለ ይመስል ቦምቡን ይዟል ተብሎ የተጠረጠረው ምስኪን ግለሰብ በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድሎና በእንጨት ግንድ ላይ ተዘቅዝቆ ተሰቅሏል። ስለነዚህ ጉዳዮች በወጣት ቡድኖች በኩል የተገለጹ ትክክለኛ ዘገባዎች እስከዛሬ ይፋ አልተደረጉም። እረ ጎበዝ፣ ወዴት እየተጓዝን ነው? ለነፃነትና ለፍትህ የተዋደቀው፣ በህይወቱና በአካሉ ቁጥር ስፍር የሌለውን ሰቆቃ ከፍሎና አሳልፎ ለዚህች የተስፋ ቀን ያበቃን ወጣት ያስገኘልንን ነፃነት እንዴት ራሱ መልሶ ሊቀብራት ይሯሯጣል? ወይስ በስሙ የሚነግዱ ሌሎች የወሮበላ ቡድኖች እየወረሩን ነው?  ነፃነት እኮ ስርአተ—አልበኝነት አይደለም፣ ህገወጥነት አይደለም፣ ነፃነት ደግሞ ነፃ አይደለም፣ መሪር ዋጋ በደምና በአካል ተከፍሎበታልና።  ልብ ያለው ልብ ይበል! እነዚህ ግብታዊና ህገወጥ እርምጃዎችስ የእነዶ/ር አቢይ አህመድንና የለውጥ ተባባሪዎቹን አላማ ያሳልጣሉ/ያፋጥናሉ ወይስ ያዘገያሉ ወይንም ደግሞ ከነአካቴው ይቀለብሳሉ? ለምንድነው እስከዛሬ እንዳሳየነው እኛ ወጣቶች ለአዲሶቹ የለውጥ አራማጅ መሪዎቻችን የአጋዥነት ድርሻችንና ሚናችንን ለመወጣት እንጂ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የመሪዎቻችን የመሪነት ተግባርና ሃላፊነት ለመሻማት ወይም ለመንጠቅ የምንሻው? እረ እየተስተዋለ፣ በስሜታዊነት ብቻ ተገፋፍተን የለውጥ አደናቃፊዎችን ተልእኮ ቀንደኛ ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች ሆነን እንዳንሰለፍ። ልብ ያለው ልብ ይበል! ይህ በዚህ እንዳለ ቢሆንም፣ በኢህአዴግ የሚመራው መንግስት በኢፌዴሪ ህገመንግስት የተሰጠውን የኢትዮጵያን ህዝብ ከውጭና ከውስጥ ጠላቶች የመጠበቅ ህገመንግስታዊ ተግባር፣ የህግ የበላይነትንና ሰብአዊ መብቶችን የማስከበር ግዴታና ሃላፊነት በምንም ምክንያት ከዘረኝነት ገና ባልፀዱና አክራሪ ብሄርተኝነት በሚያራግቡ ጥቂት አደገኛ መሪዎች ለሚዘወሩ ለጋ ወጣቶች (ቄሮዎችና ፋኖዎች) አሳልፎ መስጠት የለበትም፣ በፍፁም! በመላ አገሪቱ የተቀጣጠለውን ለውጥ ያመጣነውና የለውጡን መሪዎች ጭምር "የፈጠርናቸው" እኛና እኛ ነን፣ እኛ በምንፈልገው አቅጣጫ ካልመሩን ነገ እናወርዳቸዋለን ብለው የሚያስፈራሩትንና የመላውን ህዝብ ረጅምና መራራ ትግል በማኮሰስ ራሳቸውን ሰማይ የሰቀሉ ጥቂት ግብዝ እብሪተኞችን አደብ እንዲገዙ በስልጣን ያለው መንግስት ጥብቅ እርምጃ በአፋጣኝ መውሰድ ይኖርበታል፣ በመላው ህዝብ መካከል የሚፈጥሩት ውዥንብርና ስጋት በቀላሉ መታየት የለበትም።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ያለፉት ዘመናት ያፈጠጠ ያገጠጠ ታሪክ እንደሚያረጋግጥልን፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበረሰባዊ ቀውሶችን ተከትሎ የሚነሱ እንደአቢይ አህመድ ያሉ ገናና/ተወዳጅ መሪዎች አንዳንዶቹ  ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ቀስ በቀስ ወደሽብርተኝነት አምርተዋል፣ ለምሳሌ፣ "ነፃነት፣ እኩልነትና ወንድማማችነት" የሚሉ አማላይ የሪፎርም አጀንዳዎች አውጀው የተነሱት የ1789ቱ  የፈረንሳይ አብዮት መሪዎች በገጠሟቸው ተቃውሞዎች የተነሳ ወደጅምላ ጭፍጨፋና ሽብር /"Jacobin Terror"/ ተዘፍቀው

ብዙም ሳይቆዩ ስልጣናቸውን በአምባገነኑ መሪ በናፖሊዎን ቦናፓርቴ ተነጥቀዋል፣ አብዮቱንም ከግብ ሳያደርሱ ከሽፎባቸዋል፣ በተመሳሳይ ሁኔታ የሩሲያውን የቄሳር ኢምፓየር እስቴት ከመበታተን ለማዳን "ግልፅነት" /Glastnost/ እና "እንደገና ማዋቀር"/Perestroika/ የሚሉ የማሻሻያ አጀንዳዎችን እኤአ በ1989 አም ለመተግበር ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የነበረው ፕሬዚዳንት ሚካኤል ጎርባቾቭ አላማው ሳይሳካለት ቀርቶ የቄሳሩ ግዛተ—መንግስት ፍርክስክሱ ወጥቶ ወደ14 የተለያዩ ነፃ አገሮች ሊቋቋሙ ተገድደዋል። የተቀሩት አማላይ መሪዎች ደግሞ ወደናዚ ዘረኝነትና ወደፋሺዝም የጥፋት ጎዳና አምርተው ህዝቦቻቸውን ወዳልታሰቡ የመከራና የውድመት አዘቅቶች አስገብተዋል (ለምሳሌ፣ ሂትለር፣ ሙሶሎኒ)፣ ሌሎች ደግሞ የነፃነትና የታሪክን ጥሪ ተንተርሰው ብቅ ያሉት ገናና መሪዎች ደግሞ( እነማህተመ ጋንዲ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ኔልሰን ማንዴላ፣ ወዘተ) አገሮቻቸውን ለነፃነት፣ ለኢኮኖሚ እድገትና ለዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርአት አብቅተዋል። ስለዚህ ዛሬ በአገራችን ያለው ሁኔታ ገና በጭጋግ ውስጥ የተሸፈነ ነው። በፍፁም አልጠራም ገና። እነዶ/ር አቢይ አህመድና ጓዶቹ ገና ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮተአለማቸው አልተቆራረጡም፣ ይህ አሳሳቢ ማነቆ ነው ለመሪዎቹም ሆነ ለሁላችንም፣ ምክንያቱም ባለፉት 27 አመታት እንደተሰቃየንበት ሁሉ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የጥቂቶች የፍፁም አምባገነንነት አገዛዝ ነውና። በተጨማሪም የእነዶ/ር አቢይ አህመድና ጓዶቹ፣ "የመደመር፣ የይቅርታ፣ የፍቅርና የኢትዮጵያዊነት" ፖለቲካ በማንነት/በብሄር ፖለቲካ ላይ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነትና በዜግነት ላይ እንደሚያቀነቅን በአደባባይ ታውጆልን ሳለ "በብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሉአላዊነት" ላይ የተመሰረተው የኢፌዴሪ ህገመንግስት በህዝበ—ውሳኔ (ሬፈረንደም) ወይም በልዩ ህገመንግስታዊ ኮሚሽን አማካኝነት ተጠንቶና በፖለቲካ ሃይሎች ውይይትና መግባባት ላይ ተመርኩዞ ሳይሻሻል ወደዴሞክራሲና ወደመድበለ—ፓርቲ የምርጫ የምናደርገውን የለውጥ ጉዞ እንዴት ሆኖ ወደፊት ለማራመድ ይቻለናል? የምርጫ ወቅት 2012 እየተቃረበ ነው፣ የሁለት አመታት ጊዜ ብቻ ነው የቀረን። ታዲያ የዶ/ አቢይ አህመድን ጥሪ ተከትሎ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከመላው አለም ወደኢትዮጵያ የገቡት የተለያዩ፣ አንዳንዴም የማይታረቁ አጀንዳዎችን፣ የርእዮተአለም መርሆዎችና ፕሮግራሞችን የሚያራምዱ የፖለቲካ ድርጅቶች በጨዋታው ህጎች/ደንቦች በቅድሚያ የጋራ ስምምነት በማድረግ ያለአንዳች ግጭቶች ሰላማዊና በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት የሚኖራቸውን ምርጫዎች ለማካሄድ እንዲሁም የምርጫዎቹን ውጤቶች በፀጋ ለመቀበል ፈቃደኞች ሊሆኑ ይችላሉ ወይ? የሚለው ጥያቄ እጅግ አስጨናቂ ጉዳይ ነው፣ ካለፈው ልምዳችንና ተመክሮአችን ስንነሳ። አዎን፣ ወደዴሞክራሲያዊ የምርጫ ስርአትና ወደብልፅግና ዘመን እንደምናመራ ከተወዳጁ ወጣት መሪያችንና ከለውጥ ቡድኑ ከተበሰረልን የተስፋ መግለጫዎች በስተቀር ስለምንተማመንበት ሁኔታ ገና እርግጠኞች አይደለንም ። ዛሬ በዘልማድ "ክርስቲያኑም ሆነ ሙስሊሙ" ተስፋ አይቆርጥም እንዲሉ ሁላችንም በተስፋ መጠባበቅ ብቻ ነው፣ ወደነፃነትና ወደዴሞክራሲያዊ ጎዳና እንዲያመራም የየበኩላችንን ያላሰለሰ ትግል ማፋፋም ነው የሚጠበቅብን። ፕለቶ የሚባል የግሪክ ፈላስፋ እንደተናገረው፣ "በሰዎች የህይወት ቲያትር ውስጥ ተመልካቾች የሚሆኑት አማልክትና መልአክት ብቻ ናቸው"/"In the theatre of human life it is only for gods and angels to be spectators"...Plato/

"So many idealistic political movements for a better world have ended in mass-murdering dictatorships. Giving leaders enough power to create 'social justice' is giving them enough power to destroy all justice, all freedom, and all human dignity."
----Thomas Sowell
★"Government is not reason; it is not eloquence; it is force! Like fire, it is a dangerous servant and a fearful master."
--------George Washington